# የማዕድን ሥራ ፈቃድ ለማውጣት መሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ

## ቁጥር 274/2013 ዓ.ም

መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

## ፈቃድ ለማውጣት መሟላት ስላለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች ለመወሰን የወጣ መመሪያ

በማዕድን ዘርፍ ኢንቨስትመንት ለመሰማራት ለሚፈልጉ ፈቃድ ጠያቂዎች ፈቃድ አሰጣጥ ሁኔታዎችና የፈቃድ ዓይነቶች በማዕድን አዋጅ 52/1985 /እንደተሻሻለው/ በደንቡ 182/1986 የተደነገገ በመሆኑ፡-

በአዋጅና በደንቡ የተደነገጉትን የፈቃድ ዓይነቶችና ፈቃዱን ለማግኘት የሚያስችሉ ቅደመ ሁኔታዎችን ግልፅነትና ተጠያቂነት ባለው መልክ ለማስፈጸም የሚቻልበትን አሰራር መቀየስ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ /3/ አዋጁን ለማስፈጸም የሚያስችል መመሪያ ለማውጣት እንደሚችል በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### ክፍል አንድ ጠቅላላ

### አንቀጽ አንድ

### አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ በማዕድን አዋጅ 52/1985 እና በደንቡ ቁጥር 182/1986 የተደነገጉትን የፈቃድ ዓይነቶች ለማውጣት የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችን መሠረት በማድረግ የወጣ የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር መመሪያ ቁጥር 274/2013 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ ሁለት

### ትርጓሜ

በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985 አንቀጽ 2 እና በማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1986 አንቀጽ 2 ሥር የተተረጐሙት ቃላት በዚህ መመሪያ ውስጥ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ

**የሥራ ኘሮግራም ማለት ፡-** አዋጁን ለማስፈጸም በወጣው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ መሠረት ፈቃዱ ፀንቶ በሚቆይበት ጊዜ አመልካቹ ሊያከናውን ያቀደውን የሥራ፣ የሰው ኃይል፣ የመሣሪያ እና የወጪ መጠን ማለት ነው፡፡

**የማዕድን ማምረት ሥራ ፕሮግራም ማለት፡-** በደንቡ ቁጥር 182/1986 በአንቀጽ 5 በተደነገገው መሠረት የተዘረዘረው ማለት ነው፡፡

**የሥራ ፈቃድ ማለት ፡-** አግባብ ባለው ሕግ መሠረት የሚሰጥ የሥራ ፈቃድ ማለት ነው፡፡

**አማካሪ ማለት፡-** የማዕድን ሥራዎችን በብቃት በመረዳት ሥራውን ወይም ከሥራው ጋር ስለተያያዙ ጉዳዮች ሙያዊ ምክር፣ እገዛ እና አስተያየት የሚሰጥ ነው፡፡

የፆታ አገላለጽ

በዚህ መመሪያ በወንድ ጾታ የተገለጸው ለሴት ጾታም ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum

## አንቀጽ ሶስት

## የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ በማዕድን አዋጅና ደንብ መሠረት በማዕድን ዘርፍ የሚሰማሩ አመልካቾችን በተመለከተ ፈቃድ ከማውጣት፣ ከማደስ፣ ከዝውውርና ከማሻሻል ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ብቻ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ መመሪያው በክልል መንግሥታትም ተመሳሳይ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የፈቃድ ማመልከቻ ቅደመ ሁኔታዎች

በማዕድን ኢንቨስትመንት ዘርፍ ለመሰማራት የሚፈልግ ማንኛውም ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ስለሚያቀርበው የሥራ ፕሮግራምና የማምረት የሥራ ፕሮግራም ስለማቅረብ ቅድመ ሁኔታዎች፡፡

1. ለፍለጋ ፈቃድ

   የፍለጋ ፈቃድ አመልካቹ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ከሆነ ከማመልከቻው ጋር አያይዞ የሚያቀርበው የሥራ ሰነድ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቅድመ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል፡፡

   የሥራ ፕሮግራሙ ጥናት አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ ባለው አማካሪ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

   ከላይ በቁጥር 1.1 የተጠቀሰው አማካሪ የሥራ ፈቃድ፣ የግብር ከፋይነት ቁጥር መቅረብ አለበት፡፡

2. ለምርመራና ለማምረት ሥራ ፈቃድ

   ማንኛውም በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985 እና በማዕድን ሥራዎች የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 182/1986 መሠረት የምርመራና የማምረት ፈቃድ ጠያቂ አመልካች ከማመልከቻው ጋር አያይዞ በሚያቀርበው የሥራ ፕሮግራም እና የማዕድን ማምረት ሥራ ፕሮግራም በተመለከተ ከዚህ በታች በተዘረዘረው መልኩ መቅረብ አለበት፡፡

   2.1 ፈቃድ ጠያቂው የሚያቀርበው የሥራ ፕሮግራም እና የማዕድን ማምረት ሥራ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በተሰጠ ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ ባለው አማካሪ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

   2.2 ከላይ በቁጥር 2.1 የተጠቀሰው አማካሪ ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ እና የግብር ከፋይነት ቁጥር ከሰነዱ ጋር መቅረብ አለበት፡፡

3. ስለተጣመረ ፈቃድ

   ማንኛውም በማዕድን አዋጅ ቁጥር 52/1985 እና በማዕድን ሥራዎች ደንብ ቁጥር 82/1986 መሠረት ስለተጣመረ ፈቃድ ጠያቂ አመልካች የሥራ ፕሮግራሙን እና የማዕድን ማምረት ፕሮግራም አግባብ ባለው ሕግ መሠረት በተሰጠ ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ ባለው አማካሪ የተዘጋጀ መሆን አለበት፡፡

   ከላይ በቁጥር 3.1 የተጠቀሰውን ሰነድ ያዘጋጀው አማካሪ ሕጋዊ የሥራ ፈቃድ እና የግብር ከፋይነት ቁጥር መቅረብ ይኖርበታል፡፡



የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia Ministry of Mines and Petroleum

4. <u>በራሱ ባለሙያ የሥራ ፕሮግራም እና የማዕድን ማምረት ሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ስለሚመጣ አመልካች</u>

4.1 ማንኛውም ፈቃድ ጠያቂ አመልካች የሥራ ፕሮግራሙንም ሆነ የማዕድን ማምረት ሥራ ፕሮግራም በራሱ ባለሙያ ተሰርቶ ሲቀርብ ፦

4.1.1 የባለሙያው ሙሉ ስም፣

4.1.2 የባለሙያው ሥራ ድርሻ

4.1.3 የባለሙያው የመሥሪያ ቤት መታወቂያ ኮፒ

4.1.4 በባለሙያውና በመሥሪያ ቤቱ/በድርጅቱ መካከል የተቋቋመ የሥራ የውል ሰነድ /ቅጂ/

4.1.5 የሙያው ዓይነት ተያይዞ አብሮ መቅረብ ይኖርበታል።

4.2 የድርጅቱ ባለቤት የሥራ እቅዱን እና የማዕድን ማምረት ሥራ ፕሮግራሙን ሰርቶ ሲያቀርብ፡-

- ሙሉ ስሙ
- የሙያው ዓይነት
- የመታወቂያው ኮፒ ተያይዞ መቅረብ አለበት

5. የውጭ አገር አመልካች አግባብ ባለው በውጭ አገር አማካሪ ወይም በውጭ አገር ዜጋ ባለሙያ የሥራ ፕሮግራም ወይም ማዕድን የማምረት ሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ሲያቀርብ በዚህ አንቀጽ 4 ተ.ቁ. 4.1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሥራ ፈቃድና የግብር ከፋይነት ማስረጃ እንዲያቀርብ አይጠየቅም።

<u>አንቀጽ አራት</u>

<u>መመሪያው ስለሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ 01... /2002 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

ጥቅምት 16. ቀን 2002 ዓ.ም

የማዕድንና ኢነርጂ ሚኒስቴር
አዲስ አበባ

የማዕድንና ነዳጅ ሚኒስቴር
መዝገብ ቤት
RECORD
Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Mines and Petroleum